| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "ግጥም" ። |
| ርእስ ፤ | "ዐድዋ ፡ መልስ ። " |
| ደራሲ ፤ | በቀናው ፡ ልሳኑ ። |
| ዕለት ፤ | የካቲት ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | የዐድዋ ፡ ድል ፡ በዓል ፡ 125 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ግጥም

poem | poème | اشعار

——

ከዐድዋ ፡ ድል ፡ 125 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ።

## ዐድዋ ፡ መልስ ።

በቀናው ፡ ልሳኑ ።

——

ዐድዋ ፡ የሰርግ ፡ ዐፈር ፥ መረሬ ፣ መዘጋ ፤
የተቀላቀሏት ፡ ደም ፣ ዐጥንት ፣ ሥጋ ፤
ለድግሱ ፡ ክራይ ፡ ሲከፈላት ፡ ዋጋ ፥
ይታሰብ ፣ ይሰላ ፡ መድሎዋም ፡ አንድጋ ፤
ያን ፡ ኹሉ ፡ ዕድመኛ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አርጋ ።

የጐበዝ ፡ እፍታ ፥ የፈሪም ፡ አንቡላ ፥
በቱማታው ፡ ታየ ፥ ሲጠጣ ፣ ሲበላ ፤
ጐበዙም ፡ ረካ ፥ ፈሪም ፡ ከማጀቱ ፥
ዐቅሙ ፡ የምኒልክ ፥ ድግሱ ፡ የጣይቱ ፥
የሙሽሪት ፡ ወገን ፡ በእኩለ ፡ ቀን ፡ ፈቱ ።

ጥቍር ፡ ጤፍ ፣ ሰርገኛ ፥ አቦልሴና ፡ ማኛ ፥
ኹሉም ፡ ዐለቁና ፡ በዝቶ ፡ በላተኛ ፤
ባር ፡ ማሽላው ፡ ቀረ ፥ ጠፍቶ ፡ እንኳ ፡ ዐፍለኛ ።
የጣይቱ ፡ ድግስ ፡ ሣሣ ፤ መላ ፡ እንሻ ፤
ዛሬም ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፥ ሆድ ፡ ነው ፡ መመናሻ ።

ላገር ፡ የሚበቃው ፡ የመንግሥት ፡ ድግስ ፥
ጣይቱ ፡ ብታርብ ፥ ለእራት ፡ ሳያደርስ ፥
እጅግ ፡ ተሣቅቆ ፡ የዕድመኞቹ ፡ ዳስ ፥
ሕዝብና ፡ ሰራዊት ፡ ተማማሉ ፡ ነፍስ ፤
ሲነጋም ፡ ደገሱ ፡ ዳግም ፡ ዐድዋ ፡ መልስ ፨


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።